RESEARCH ICT AFRiCA

# ቴሌኮምኒኬሽንን ወደ ግል የማዘዋወር ስልት

(“Steps and Issues of Privatization of the Telecom Sector in Ethiopia” በሚል በዶ/ር ሊሻን አዳምና ዶ/ር አሊሰን ጊልዋልድከተፃፈው የተወሰደ)ዋናውን ሪፖርት በwww.researchictafrica.net ይመልከቱ

**Authors : Dr. Lishan Adam and Dr. Alison Gillwald**

**Contact : lishan@ictfd.net and agillwald@researchictafrica.net**

**Date : January 24, 2019**

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን በመንግስት ሞኖፖሊ ከተያዘባቸው ከአምስት የማይበልጡ ጥቂት አገሮች አንዷ ናት፡፡ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት በግል ከሚሰጥባቸው ብዙ አገሮች እንደ ጎረቤቶቻችን ኬንያ ሶማሊያና ሱዳን የመሳሰሉት ያለው ዕድገት የሚያሳየው ይህ ዘርፍ ከመንግስት ይልቅ በግል፣ ከሞኖፖሊ ይልቅ በውድድር ላይ ቢመሰረት በጥራቱና በተደራሽነቱ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፡፡

በአዲስ የለውጥ ምዕራፍ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ መንግስት የቴሌኮሚኒኬሽኑን ዘርፍ ወደ ግል ለማዛወር ዕቅድ እንዳለው ገልጿል፡፡ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ገለፃ ይህ የማዛወር ሂደት የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ እንደሚካሄድ፣ በተለይም መንግስት ከፍተኛውን ድርሻ (Golden Share) በመውሰድ የግል ባለሀብቶች የሚያደርሱትን ተፅዕኖ እንደሚቋቋምና በዘርፉ ልምድ ያካበቱ የግል ካምፓኒዎች ብቻ እንደሚሳተፉ ነው፡ ፡ለዚሁም እንዲመቻች ዘንድ ሃያ አንድ አባላት የሚያካትት የመንግስትን ሀብትን ወደ ግል ለማዛወር የሚያደርገውን ጥረት የሚከታተል ካውንስል በነሃሴ ወር ተቋቁሟል፡፡ በተጨማሪም መንግስት የቴሌኮም ህግን በማርቀቅና አዲስ የቴሌኮም ተቆጣጣሪ ድርጅት በማቋቋም ላይ ነው፡፡

ቴሌኮሚኒኬሽንን ወደ ግል የማዛወር እንቅስቃሴ በጣም ከፍተኛ ትኩረት ከሳቡት የመንግስት የቅርብ ለውጦች አንዱ ነው፡፡ ከጀርመኑ የቲ-ሞባይል (T-Mobile) ግሩፕ ጀምሮ እስከ ደቡብ አፍሪካው ኤም. ቲ. ኤን.(MTN) እንዲሁም የተለያዩ የአውሮፓና የኤስያ የቴሌኮም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ የቴሌኮሚኒኬሽን ገበያ ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከአንድ መቶ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ያላትና ኢኮኖሚዋ በፍጥነት እያደገ ካሉ አገሮች አንዷ ናት፡፡ በቴሌኮሚኒኬሽንና በፋይናንሱ ዘርፍ ምንም ትስስር የማይታይበት አገር እንደመሆኗ መጠን የተቀላጠፈየቴሌኮም እድገት ድህነትን ለመቀነስና የሥራ ዕድል በመፍጠሩ ረገድ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ እድገት በእጅጉ ያንቀላፋውን የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከማነቃቃቱም በላይ እንደ አካውንቲንግ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ማኔጅመንት የመሳሰሉትን ዘርፎች ስለሚያበረታታ በመቶዎች ለሚቆጠሩ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን የሥራ እድል ለማመቻቸት ብሩህ ተስፋ ይሰንቃል፡፡

ይህም ሆኖ ግን በአገራችን አሁንም የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ በመንግስት ስር ሆኖ የሚያድግ የሚመስላቸው እንዲያውም ወደ ግል መዛወሩን በጥብቅ የሚቃወሙ ወገኖች አሉ፡፡ ቴሌኮሚኒኬሽን "እንደምትታለብ ላም" የሚያዩና ኢትዮ ቴሌኮም በጣም አትራፊ ድርጅት የሚመስላቸው የአገሪቷን ዘርፈ ብዙ እድገት አንቆ የያዘውን የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ በመንግስት እጅ ማቆየት አገልግሎቱን ለማስፋፋት እንደሚረዳና የግል ዘርፉ ትርፍ ላይ ብቻ እንደሚያተኩር ይሰብካሉ፡፡ እስከ ዛሬ የታየው ልምድ ግን በግል የተያዙና ጥሩ የመንግስት ተቆጣጣሪ ክትትል ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ በተደራሽነቱ፣ በጥራቱና አቅምን ባማከለ ታሪፍ በመንግስት ከሚተዳደረው የተሻለ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውን በማነቃቃት ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ቴሌኮም እድገት

ከዝቅተኛ ደረጃ የተነሳው የቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ ባለፉት አስርት አመታት ጥሩ እድገት አሳይቷል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በ1994 እና በ2005 ከቻይና መንግስት የተበደረውን 3.1 ቢሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የሞባይል ተጠቃሚዎችን ቁጥር በእጅጉ ከማሳደጉም በላይ ከ6000 ኪ.ሜ በላይ መሬት ውስጥ የተቀበረ ፋይበር በመዘርጋትአገሪቷን በዘመናዊ የኮሚኒኬሽን መስመር ለማዳረስ ጥረት አድርጓል፡፡ የኢትዮ ቴሌኮም ድህረ ገፅ እንደሚያሳው የሞባይል ሲም ካርድ የገዙ ደንበኞች ቁጥር 65.7 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ወደ 40 ሚሊዮን የሚጠጉ እውነተኛ የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡ ወደ 18 ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑት ሲም ካርዶች እንደገና ለገበያ የሚውሉ ናቸው፡፡ በዚያኑ ልክ የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር አድጓል፤ ከሞባይል ተጠቃሚዎች ግማሾቱ (ወደ 20 ሚሊዮን የሚሆኑት) የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡

የሞባይልና የኢንተርኔት አገልግሎት 92 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮ ቴሌኮም አመታዊ ገቢ የሚያስገኙከመሆናቸውም በላይ በፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ በገቢ አንፃር ሲታይ ምንም እንኳን የኢትዮ ቴሌኮም አመታዊ ገቢ እያደገ ቢመጣም በአንፃራዊነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ በ2010 የኢትዮ ቴሌኮም ገቢ 38 ቢሊዮን ብር (1.4 ቢሊዮን ዶላር) ሲሆን የሳፋሪ ቴሌኮም ገቢ 2.1 ቢሊዮን ነበር፡፡ ይህም ማለት የኬኒያው ሳፋሪ ኮም በ29.5 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች ብቻ፤ከ65 ሚሊዮን ተጠቃሚ ያለውን የኢትዮጵያውን ቴሌኮም ካምፓኒ በአንድ ነጥብ አምስት እጥፍ በልጦታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ንፅፅር የኢትዮ ቴሌኮም ገቢ በሶስት እጥፍማደግ ነበረበት፡፡ በተጨማሪ ምንም እንኳን የኢትዮ ቴሌኮም ገቢ ብዙ ቢሆንም የካፒታልና ኦፕሬሽን ወጪውን ቀንሶ ስለማያሳውቅ ትክክለኛው የተጣራ ትርፍ (Free Cash Flow ) ባለመታወቁ ትርፋማነቱን ለማወቅ ያዳግታል፡፡ በቴሌኮም ዘርፍ የገቢና የወጪ ስሌት የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

- አጠቃላይ ወይንም የጅምላና የችርቻሮገቢ
- የከዋኔወጪ
- ካፒታል ወጪ(የቻይና ዕዳና በየጊዜው ኔትወርኩን ሽፋን ለማሳደግ የሚወጣው ወጪ)
- ግብር
- የተጣራ የገንዘብ ፍሰት(Free Cash Flow)




እስካሁን የኢትዮ ቴሌኮም ለህዝብና ለፓርላማ የሚያሳውቀው አመታዊ ገቢውን ብቻ ነው፡፡የአንድ ቴሌኮም ድርጅት ትርፋማነትየሚታወቀው በተጣራ የገንዘብ ፍሰቱ (Free Cash Flow) ነው፡፡ የተጣራ የገንዘብ ፍሰት ለሚሸጠው ኢትዮ ቴሌኮም ዋጋ ግምት መሰረታዊ ከመሆኑም በላይ እውነተኛ ትርፋማነቱንና ዕድገቱን መለኪያ በመሆኑ ይኸው ቀመር ተሰርቶ ለህዝብና ለፓርላማ መታወቅ አለበት፡፡

## የቴሌኮም ወደ ግል የማዛወር ጥቅሞች

በጠቅላይ ሚኒስትሩ አገላለፅ ቴሌኮሚኒኬሽን ወደ ግል የማዛወር ዋና ምክንያት እያሽቆለቆለ የመጣውን የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ማዳን ከተቻለም ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ነው፡፡ ምንምእንኳ የውጭ ምንዛሬ መሰረታዊ ምክንያት ቢሆንም የኢትዮ ቴሌኮም ወደ ግል የማዛወር ስራ ኢኮኖሚዉን በተሻለ ደረጃ የሚያሳድግና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፉንየሚያነቃቃ የቴሌኮም ስርአትን ለመገንባት መሆን አለበት::በተጨማሪ ወደ ግል የማዛወር ሂደቱ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል፡፡

1ኛ/ **የመንግስት እዳን መቀነስ ፤**የኢትዮጵያን እዳ ወደ 29 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ10% የሚበልጠው (3.1 ቢሊዮን ዶላር) ለቴሌኮም አገልግሎት የተበደረችው ነው፡፡ የቴሌኮም ወደ ግል መዛወር የሚቀጥለውን ብድር ከመግታቱም በላይ ከሽያጩም የሚገኘው ገቢ የአገሪቱን አጠቃላይ ብድር /እዳ/ ለመቀነስ ይረዳል፡፡

2ኛ/ **አመራሩንና አሰራሩን ቀልጣፋ ማድረግ፤** የቴሌኮም ወደ ግል መዛወር የድርጅቱን አመራር ወደ ግል አመራር ዘይቤ ስለሚቀይረው ቀልጣፋ አመራርና አገልግሎት እንዲሰጥ ይረዳዋል፡፡

3ኛ/ **የቴሌኮም ተደራሽነትና ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ ለማግኘት፤** የቴሌኮም ወደ ግል መዛወር አዳዲስ ኢንቨስትመንትና ቴክኖሎጂን ስለሚያበረታ ተደራሽነቱ እየሰፋ በዛውም ልክ ተመጣጣኝነቱና ጥራቱም እያደገ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

4ኛ/ ቴሌኮምን ወደ ግል ማዛወር የአገልግሎቱን ተወዳዳሪነት ያበረታታል፡፡

የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት ከመንግስት ሞኖፖሊ ወደ ግል የማዛዋወሩ ስራ በጥንቃቄ መስራት አለበት፡፡ እንደውም በተቻለ መጠን መንግስት የሴክተሩን ተወዳዳሪነት (Competition) ካልፈጠረ በስተቀር ቴሌኮምን ወደ ግል ማዛወሩከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡ ከዚሁ ጎን መታየት ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ የዜጎችና የአገሪቱ መረጃ ደህንነት በአስተማማኝ ሁናቴ መጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት በዝውውሩ ጉዳይ ህዝቡን፣ ምሁራንና፣ የሲቪል ማህበረሰቡን ማሳተፍ አለበት፡፡

## ቅድመ ሁኔታዎች

መንግስትቴሌኮምን ወደ ግልሲያዛውርየሚተሉትን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1. ለህዝቡ ስለ ቴሌኮምን ወደ ግል የማዘዋወር ስራ ጥቅም፣ ጉዳትና ጠቅላላ ሒደቱ ቀጣይና ተከታታይ መረጃ መስጠት አለበት፡፡ የዝውውሩሂደት ለህዝቡ፣ለድርጅቱ ሰራተኞች ለኢንቬስተሮች፣ ለተፎካካሪ ፓርቲዎችና፣ ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ማሳወቅ ግልፅነቱን ከማስፈኑም በላይ ሂደቱን ከሙስናና ከብልሹ አሰራር ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
2. ወደ ግል ለማዘዋወር የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎች (Sector Law) ማደራጀት፤ ከነዚህም የህግ ማእቀፎች መካከል አዲስ የቴሌኮም ህግ ማውጣት አንዱና ዋናው ወሳኝ ሒደት ነው፡፡ ይህ የቴሌኮም ህግ ከሚያካትታቸው ነገሮች አንደኛው አዲስ የቴሌኮም ተቆጣጣሪ (Regulator) ማቋቋም፣ ሁለተኛው የቴሌኮም አገልግሎት አፈቃቀድ ስርዓት፣ በቴሌኮም ዘርፍ ተወዳዳሪነት ማፍራት ፣ (Competition) በተወዳዳሪዎች፣ መካከል ያለውን ግንኙነት ስርአት ማስፋፋት (Inter connectivity)እና አስፈላጊ የሆኑትን መሰረተ ልማት (infrastructure) ለማሟላትየሚደረገውንጥረት ሁሉ ማካተት አለበት፡፡
3. አዲሱ የቴሌኮም ህግ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣በቴሌኮሚኒኬሽንና በፖስታ፣በብሮድካስት (በቴሌቪዥንና ሬድዮ) በመሳሰሉት መካከል ያለዉን ግንኙነት (Convergence) ባማከለ መልኩ መደራጀት አለበት።

   ሌሎች በህጉ ታሳቢ መሆን ካለባቸው ጉዳዮች መካከል ፣

   - የዋጋ ተመን (Tariff) ስርዓት
   - የሞገድ (Frequency) አጠቃቀም ስርዓት
   - የሸማቹን መብት ማስጠበቅና (Protection) የቅሬታ አፈታት ስርዓት
   - በዘርፉ የሚደርሱ እና ጥፋቶችንና የህግ ጥሰት ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት የመሳሰሉት ናቸው፡፡
4. ከንግድ ዘርፍ ጋር የተያያዙ ህጎች ለምሳሌ (Commercial Code) አዳዲስ የአክሲዮን ገበያ ህጎች ማሻሻልና ማደራጀት፡፡
5. ኢትዮቴሌኮምን በአዲስ መልክ ማዋቀር ፣ ይህ ማለት መንግስት የቴሌኮምን ሰርቪስ ወደ ግል ከማዘዋሩ በፊት በተሻለ መንገድ መልሶ ቢያዋቅረውና ወዲያውኑ በተቀላጠፈ አመራር ስር ቢያውለው ወደ ግል በሚዛወርበት ጊዜ ጥሩና የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣ ይረዳዋል፡፡
6. አዲስ የቴሌኮም አገልግሎት ዘርፍ ተቆጣጣሪ (Regulatory Agency) ማቋቋም ፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በዚህ ዘርፍ የተደራጀና በቂ ክህሎት ያለው ተቆጣጣሪ ድርጅት ባለመኖሩ በዚህ ዘርፍ ብዙ ስራ ይጠበቅባታል፡፡ እንደ ግብፅና ናይጄሪያ ያሉት አገሮች ከ500 በላይ የሚበልጡ ባለሙያዎች ያሉባቸው በጣም የተቀላጠፈ እጅግ ዘመናዊ የሆነ ተቆጣጣሪ መ/ቤት አላቸው፡፡ይህን ተቆጣጣሪ መ/ቤት በአጭር ጊዜ ለማቋቋም ከ100 በሚበልጡ ከተለያዩ ሙያ ማለትም ከህግ ፣ከኢኮኖሚክስ ፣ማኔጅመንት እና ከተለያዩ አስፈፃሚ አካላት በተወጣጡ ባለሙያዎች ማዋቀር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች አገሮች ካሉ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ክህሎትን ማዳበር የግድ ነው፡፡ የቴሌኮም ቁጥጥር ስራ የቴክኖሎጂ ስራ ብቻ ስላልሆነ ይህን መ/ቤት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች መሙላት አይጠቅምም፡፡
7. የውድድሩን ምህዳር መዘርጋት፤የቴሌኮምን ወደ ግል ማዛወርበውድድር ካልታገዘ ብቻውን ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡ይህም ማለት የተለያዩ የቴሌኮም ዘርፎችን በሂደት ለውድድር ክፍት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡እንደ ኢንተርኔትና ሞባይል አገልግሎቶች በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ለውድድር መከፈት አለባቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች በቅደም ተከተል መተግበሩ የተለየ ፋይዳ አለው፡፡ በሌሎች አገሮች ያለው ልምድ እንደሚያሳየው ከቴሌኮም ሕግ በመቀጠል አዲስ ተቆጣጣሪ ድርጅት ማደራጀቱ የቴሌኮምን ወደ ግል ለማዛወር ፋይዳ አለው፡፡ መንግስት የኢትዮቴሌኮምን ወደ ግል ካዛወረ በኋላ በአፋጣኝ የኢንተርኔትና የሞባይልን አገልግሎት ለተወዳዳሪዎች መክፈት አለበት፡፡ ይህም ከመንግስት ሞኖፓሊ ወደ ግል ምኖፖሊ የማዘዋወሩን አዝማሚያ ከማቆሙም በላይ የቴሌኮም ዘርፉ ለማህበረሰቡና ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅዎ ለማሳደግ ስለሚረዳ ነው፡፡ በቴሌኮም ዘርፍ ተወዳዳሪነት (Competition) መስፋፋት አዳዲስ ፈጠራዎችን፣ ተጨማሪ አቅም፣ የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ያስፋፋል ተብሎ ይገመታል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ወደ ግልበሚዘዛወርበትግዜ ሊሰሩ ከሚገቧቸዉ ስራዎች መካከል የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ/ **መልሶ ማቋቋም (Restructuring)**፤ኢትዮ ቴሌኮምን በአዲስ መልክ አስቀድሞማዋቀር  ለግሉ ዘርፍ በሚያመች መልኩ በማደራጀት ከሽያጩ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ የዚህ ስራ በዘርፉ የቴሌኮም ድርጅቶችን በአዲስ መልክ በማዋቀር የተካኑ ባለሙያዎች ቢደገፍ ይመረጣል፡፡

ለ/ የኢትዮ ቴሌኮምዋጋ ተመን ፤ የዋጋ ትመና ስራ (Valuation) በከፍተኛ ጥንቃቄ መስራት ያለበት ከመሆኑም  በላይከሶስት በላይ የሆኑትን የትመና ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡የብዙ አገር ልምዶች እንደሚያሳየው ከሁለትና ሶስት በላይ በሆኑ የትመና ዘዴዎችን መጠቀም  ጥሩ ነው፡፡ ስለዚህም መንግስት በብዛት ጥቅም ላይ የዋሉትን እንደ፣

- Discounted Cash Flow Method
- Relative Valuation Method
- Balance Sheet Method

የመሳሰሉትን የቴሌኮም ካምፓኒ ዋጋ ትመና ዘዴዎችበመጠቀም የተገኘውን የዋጋ ተመን በመመርኮዝ ኢትዮቴሌኮምን ከመንግስት ወደ ግል ዘርፍ ማሸጋገር አለበት፡፡ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀሙ ሂደቱ ግልፅና ከተጠያቂነት የሚያድን ከመሆኑም በላይ ለሃገሪቷም በተገቢው መንገድ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ያስከብራል፡፡ ይህም ማለት መንግስትና በትመናው ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ቅድመ መረጃ በማሰባሰብ፣ የተለያዩ የትመና ዘዴዎችን በማጣመር የኢትዮቴሌኮምን ዋጋግልፅ በሆነ መንገድ ለህዝቡና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ አለባቸው፡፡

ሐ/ የሽያጩ ሒደት (Transaction) የሽያጩ ሂደት ትክክለኛ የጨረታ ሰነዶች በማዘጋጀት ገደቦችን በማውጣትተጨማሪ ማብራሪያዎችን ለተሳታፊ ድርጅቶች መስጠትንና በመጨረሻም ላሸነፈው ድርጅት ባለማመንታት ሽያጩን ማስተላለፍ ይጠይቃል፡፡

## ኢትዮቴሌኮም ወደ ግል ከተዘዋወረ በኋላ መሰራት ያለባቸው ስራዎች

ቴሌኮምን ወደ ግል የማዛወሩ ስራ እንደ ሂደት መታየት ያለበት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህም ወደ ግል ከማዛወሩ በፊት የነበሩ ስራዎች ለምሳሌ የተቆጣጣሪ መ/ቤቱን ክህሎት በማሳደግና በቴሌኮሙ ህግ መሰረት በኢንተርኔትና በሞባይል በመሳሰሉት አገልግሎቶች ተወዳዳሪነትን (Competition) የማስረፅ ስራ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ መንግስት ኢትዮ ቴሌኮምን ወደ ግል ከማዛወሩ ለጥቆ አዲስ ሁለተኛ የሞባይል አገልግሎት ስራ (2nd National Mobile Operator) የመፍቀድ ስራ ቢሰራ ጠቃሚ ነው፡፡ አዳዲስ ድርጅቶች ወደ ገበያ በገቡ ቁጥር የመቆጣጠሩ (Regulation) ስራ በዛው መጠን ስለሚሰፋየተቆጣጣሪ መ/ቤቱን በሰው ሃይልና በክህሎት የማደራጀቱ ስራ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

በቴሌኮም ዘርፍ የሚደረጉ ምርምርና ስርፀት (Research and Development) ማስፋፋት ከዝውውሩ በኃላ መደረግ ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ምርምርና ስርፀት ወደ ፊት የቴሌኮሚኒኬሽንእድገትን  አቅጣጫ ለመወሰን ከመርዳቱም በላይ የመንግስት ፖሊሲ በእውቀትና በምርምር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይረዳል፡፡